1. ጌታ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 7 የነበረውን ሰው እንዴት ፈወሰው?
ሀ) ጣቶቹን ወደ ጆሮው አግብቶ
ለ) ምራቁን እንትፍ ብሎ ምላሱን ዳሰሶ
ሐ) ወደ ሰማይ ተመልክቶ "ኤፍታህ " ብሎ
መ) ሁሉም

2. እጅን ታጥቦ እህል መብላት ከሚከተሉት ውስጥ ከየትኛው ይመደባል?
ሀ)ትዕዛዘ እግዚአብሔር
ለ)የሽማግሌዎች ወግ
ሐ)ስርዓተ መላእክት
መ)ሁሉም

3. ፈሪሳውያን ካላጠቡ የማይጠቀሙት ነገር ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) እጃቸውን ለ) ጽዋቸውን ሐ) ድስታቸውን መ) መልሱ የለም"

4. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ሰባት ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያንን ስለምን ገሰፃቸው
ሀ) ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ይልቅ የሰውን ወግ ስለሚያጠብቁ
ለ)ከሰው ወግ ይልቅ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለሚያጠብቁ
ሐ) እጃቸውን ታጥበው ስለማይበሉ
መ)ሁሉም

5. ከሰው የሚወጣው እሱም ሰውን ያረክሰዋል " የተባለው ምንድነው?
ሀ) ዝሙት ለ) መግደል ሐ) መስረቅ መ) ሁሉም

6. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ጌታ ባርኮ አብዝቶ ያበላቸው ስንት እንጀራ እና ስንት ዓሣ ነው?
ሀ) 5000 እንጀራ እና ዓሣ
ለ) 7 እንጀራ እና ጥቂት ዓሣ
ሐ) 4000 እንጀራ እና ዓሣ
መ) 5 እንጀራ እና 2 ዓሣ

7. ጌታችን በቤተሳይዳ የፈወሰው ዕውር እና ሁለት ጊዜ ተዳስሶ መፈወሱ የምን ምሳሌ ነው?
ሀ) ዕውር የመላእክት፣ ሁለት ጊዜ መዳሰሱ ሁለት ጊዜ የመፈጠራቸው
ለ) ዕውር የባሕታውያን፣ ጥቂት ጸጋ ቢሰጣቸው ሰውን ሁሉ በግዕዛ እንስሳ እንደሚያዩ፣ ፍጹም ጸጋ ቢሰጣቸው ጻድቁንም ኃጥኡንም
ሐ) ሳይለዩ ሁሉን መውደዳቸው ዕውር የፀሐይ፣ ሁለት ጊዜ መዳሰሱ ብርሃን ሁለት ጊዜ ስለመፈጠሩ
መ) መልሱ የለም

8. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ሰባት ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልጂን ያዳነላት ሴት ለምን ነበር
ሀ) ስለአለባበስዋ
ለ)ስለትህትናዋ
ሐ)እራሷን ከፍ ስለማድረጓ
መ)ለ እና ሐ

9. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ጌታ የመገበው ምን ያህል ሰዎችን ነበር?
ሀ) 7000 ከሴቶች እና ከሕፃናት ውጪ
ለ) 5000 ከሴቶችና ከሕፃናት ውጪ
ሐ) 4000 ከሴቶች እና ከሕፃናት ውጪ
መ) 3000 ከሴቶች እና ከሕፃናት ውጪ

10.በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ጌታ ሐዋርያትን "ሰው እኔን ማን ይለኛል?" ብሎ የጠየቃቸው በየት ነበር?
ሀ) በጥብርያዶስ ለ) በገሊላ ባሕር ሐ) በፊልጶስ ቂሣርያ መ) በደብረ ታቦር

11. ጌታ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ካበላቸው በኋላ የተረፈው ምን ያህል ነበር?
ሀ) 12 ቅርጫት
ለ) 5 ቅርጫት
ሐ) 7 ቅርጫት
መ) ምንም አልተረፈም

12.ጌታ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ከተናገራቸው መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) "ሰው ለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?"
ለ) "ሙሽራውን የእነርሱ ለይተው የሚወስዱበት ቀን ይመጣል፤ ያን ጊዜም ይጾማሉ። "
ሐ) "ሊከተለኝ የሚወድ ሰው ራሱን ይካድ፤ ጨክኖም የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ። "
መ) "በእኔና በቃሌ የሚያፍረውን ሁሉ የሰው ልጅም በአባቱ ክብር ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ በመጣ ጊዜ ያፍርበታል። "

13.ጌታ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ላይ ዕውሩን ሰው ዳሰሶ የፈወሰው በየት ነበር?
ሀ) በፊልጶስ ቂሣርያ ለ) በቤተሳይዳ ሐ) በቤተልሔም መ) በጥብርያዶስ ዳርቻ

14.በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 8 ሐዋርያት ወደ ታንኳ ሲገቡ ...
ሀ) ምንም እንጀራ አልያዙም ነበር
ለ) አንድ እንጀራ ይዘው ነበር
ሐ) ለሁላቸውም የሚበዛ ምግብ ይዘው ነበር
መ) መልሱ የለም

15."እነዚህ ሕዝቦች በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው ግን ከእኔ በጣም ይርቃሉ። የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርትን እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል። " ያለው ነቢይ ማን ነበር?
ሀ) ኤርምያስ ለ) ኢሳይያስ ሐ) አሞጽ መ) ዘካርያስ

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ እና በቃሉ የሚያፍሩትን ምን ዋጋ እንደሚጠብቃቸው ተናገረ
ሀ)የዘላለም ሕይወት
ለ)በአባቱ ፊት ይመሰክርላቸዋል
ሐ) በአባቱ እና በመላእክት ፊት ያፍርባቸዋል
መ)ሁሉም

17.ጌታችን ጴጥሮስን "አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ሂድ፤ እንቅፋት ሆነህብኛል " ያለው ለምንድን ነው?
ሀ) ጌታ አይሙት ማለት ነቢያትን ሐሰተኞች ማድረግ ስለሚሆን ነው
ለ) በጴጥሮስ አንጻር ሰይጣንን ሲገሥጽ ነው
ሐ) ጴጥሮስን ከሐዋርያት ለይቶ ሲያወግዝ ነው
መ) ሀ እና ለ

18.ኤፍታህ ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ) ተከፈት ለ) አውራ ሐ) ተገለጥ መ) ተዘጋ

19.ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊከተለው የሚወድ ምን ያድርግ
ሀ)ራሱን ይካድ
ለ)የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ
ሐ)ዓለምን ይግዛ
መ)ሀ እና ለ

20. ሰው እኔን ማን ይለኛል ለሚለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥያቄ ሐዋርያት የሰጡት መልስ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ክርስቶስ
ለ) መጥመቁ ዮሐንስ
ሐ) ኤልያስ
መ)ሁሉም